የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

ጥር 17 ቀን 2013 ዓ.ም.

# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ የፕሬስ መግለጫ

በመላ አገሪቱ ሲካሄድ የነበረው ነገር ግን በሕግ የማስከበር ዘመቻ ምክንያት በትግራይ ክልል የተቋረጠው የብር ቅያሪ ሥራ ከታህሣሥ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለ14 ቀን መራዘሙ ይታወሳል።

ሆኖም የተራዘመውን ጊዜ አተገባበር በተመለከተ ከተለያዩ ወገኖች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ተከትሎ በጉዳዩ ዙሪያ ግልፅነትን መፍጠሩ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል።

በእስካሁኑ የክልሉ የብር ቅያሪ አፈጻጸም ግምገማ መሠረት የተራዘመው ጊዜ ለእያንዳንዱ የባንክ ቅርንጫፍ የተሰጠ መሆኑ ቀርቶ ለእያንዳንዱ የክልሉ ከተማ እንዲሆን ተደርጓል።

በመሆኑም ከዛሬ ጥር 17 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በትግራይ አንድ ከተማ ቀድሞ አገልግሎት የሚጀምር የባንክ ቅርንጫፍ ሲኖር የዚያ ከተማ የተራዘመው የብር ቅያሪ ጊዜ የሚቆጠረው ይኸው የባንክ ቅርንጫፍ በከተማው ቀድሞ ሥራ ከጀመረበት ቀን እንስቶ ለ14 ቀናት ብቻ ይሆናል።

ዘግይተው ሥራ የሚጀምሩ ሌሎች የባንክ ቅርንጫፎች በከተማው አሮጌ ብር መቀየር የሚችሉት በዚሁ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል። በመሆኑም መቀሌን ጨምሮ የብር ቅያሪ ከተጀመረ 14 ቀናት ባለፋቸው የትግራይ ከተሞች ሲሰጥ የነበረው የብር ቅያሪ አገልግሎት ከዛሬ ጀምሮ የሚቋረጥ ይሆናል።

ስለዚህ በየትኛውም የክልሉ ከተማ የሚገኝ ህብረተሰብ ይህን ተገንዝቦ በተጠቀሱት 14 ቀናት ብቻ በከተማው ወደሚገኙ የባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ የአሮጌ ብር ቅያሪ አገልግሎት እንዲያገኝ ለማሳሰብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ